ምዕራፍ አንድ

የነገረ አበው መግቢያ

1.1 ምንነት

በአሁን ዘመን ያሉ ብዙዎች የክርስቲያን ወገኖች ስለ ጥንታዊቷ ቤተክርስቲያን የማወቅ ፍላጎታቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል። የአበውን ታሪክና ትምህርቶቻቸውን ማጥናት በዚያ ላይም መመራመር የብዙዎችን ትኩረት እየገዛ መምጣቱ ለዚህ አንዱ ማሳያ ነው። በጥንታዊት ቤተክርተያን ታሪክ የምናቃቸውን አባቶች ታሪካቸውን ማወቅ በራሱ ስለ ጥንታዊቷ ቤተክርስቲያን አምልኮት ÷ ማኅበራዊ ሕይወት ÷ ምግብና እና አጠቃላይ የመንፈሳዊ ሕይወት ታሪክ በቀላሉ ለመረዳት ያስችላል። በየዘመኑ ከተነሱ ጣዖት አምላኪዎች እና ቤተክርስቲያንን በፍልስፍና ትምህርት ሥር ለመጣል ከተነሱ ሰዎች ጋር ያደረገችውን ተጋድሎ ፤ በዚህም አምላካዊ ፍቅርን ሰው በመሆኑና በሞቱ የገለጠ ራሱ ክርስቶስን በመምሰል በጥላቻ አልጫ የሆነውን ዓለም በፍቅር ፤ በክህደት ጨለማ ውስጥ የተቀመጠውን በሃይማኖት ብርሃን እያሸነፈች ከዘመን ዘመን መሸጋገሯን በቀላሉ ለመረዳት ያስችላል።

ነገረ አበው ስንል ከሐዋርያት በኋላ በመነሳት ሐዋርያት በመሰከሩት ምሥክርነት ÷ ባስተማሩት ትምህርት እና ባወረሱዋቸው ሥርዓተ አምልኮት በመፅናት ከመንፈስ ቅዱስ በሆነው ትምህርታቸው ብርሃንነታቸውን እስካሁን ድረስ ላለው ክርስቲያን ሁሉ የደረሰ የአባቶች ነገር ማለታችን ነው። ይህ ትምህርት የቤተክርስቲያን አበው ሕይወታቸውና ትምህርቶቻቸው የሚቃኝበት ነው። ከዚህ ባለፈ በዓለም ሆነው የዓለምን ፍልስፍና የረቱበትን ፊሊጥ የምንረዳበት ነው።

ሀ ◦ <u>የአባቶች ሕይወት</u>፡- ክርስትና ማለት ክርስቶስን የመምሰል ሕይወት መሆኑ ነገሩ የታወቀ ነው። አበውም በየዘመናቸው ስለ አንዲት እውነት (ስለ ሃይማኖት) መከራን ሁሉ በመታገስ በተቀበሉት መከራ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን መስለውታል። ከዚህም በተጨማሪ አበው የጻፏቸውን ጽሑፎች እና የተናገዋቸውን አባባሎች በተገቢው መንገድ ለመረዳት የኖሩበትን አካባቢ ÷ ባህል ÷ ቋንቋ እና ማህበራዊ ሁኔታዎችን ማጤን

ይገባል።

ለ ◦ <u>ሥራዎቻቸው</u>፡- በየዘመኑ የተነሱ አባቶች ጽሁፎቻቸው ÷ ከሰዎችጋር ያደረጉአቸው ንግግሮች እና በመንፈሳዊ ምግባራት መጽናታቸው በሰፊው የሚጠናበት ትምህርት ነው።

ሐ. <u>አስተሳሰባቸው</u>፡- በጽሁፎቻቸው ውስጥ የሚገኙ ስለ እግዚአብሔር ÷ ስለ ሰው ÷ ስለ እግዚአብሔርና ስለ ሰው ግንኙነት እና ስለሌሎች ጉዳዮች ያለውን አስተሳሰባቸውን በአትኩሮት መመልከትና መረዳት የሚቻለው ከነገረ አበው ትምህርት ነው።

ነገረ አበው ወደ ቤተክርስቲያን ገብቶ የእርሷን መንፈስ ለማግኘት የሚረዳ በር ነው። ይህ ትምህርት ያለፉትንና የሚመጡትን ትውልዶች አንድ የሚያደርግ ነው። ይኸውም ከዘመናት በፊት የነበሩትን አባቶች መንፈሳዊ ተሞክሮዎች ÷ ትምህርቶችና ፅንሰ ሐሳቦችን ÷ አሁን ዓለም ያለበትን ሁኔታ በማገናዘብ ለትውልድ እንዲጠቅም ማስቻሉ ነው።

የነገረ አበው አስፈላጊነት

ነገረ አበው አንዱ የነገረ መለኮት ክፍል ሆኖ ብቻውን የሚጠና አይደለም። ለሁሉም የነገረ መለኮት ትምህርት ዘርፎች መሠረታዊ ትምህርት ስለሆነ ጥቅሙን መወሰን አይቻልም።

1 ◦ <u>ቅዱሳት መጻሕፍትን በትክክል ለመረዳት</u>፡- መጽሐፍ ቅዱስ (አሥራው መጻሕፍት) ገንዘብነቱ የቤተክርስቲየን መሆኑ የሚታወቅ ነው። በመሆኑም ከእግዚአብሔር በተቀበለችው መንፈሳዊ ሕይወቷ ቤተክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን ትተረጉማለች። የመጽሐፍ ቅዱስ መሰጠት ዓላማወውንና በውስጡ የያዛቸው የተለያዩ የነቢያትና የሐዋርያት መጽሐፍት የሃሳብ ስምምነትን በአበው አንደበት ታስተምራለች። ብዙዎች አባቶች መጽሐፍ ቅዱስን በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት መተርጎመቻው ለነገረ አበው ትምህርት ትልቅ መነሻ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ማለት የማይወሰነው የእግዚአብሔር ሃሳብ በሚወሰነው የሰው ቋንቋ የተጻፈ ማለት ሲሆን በየዘመናቱ የተነሱ አበው ይህን በመረዳት የመጽሐፍ ቅዱስን የተለያዩ ቃላትና ታሪኮችን በብዙ ጎበረ መልክዕ በመመልከት ተርጉመዋል።የጻፉዋቸው ትርጓሜያት የአባቶችን አስተሳብና አስተምህሮ ለመረዳት

የሚያስችሉ ናቸው። በሌላ አገላለጽ ነገረ አበውን ማጥናት ቅዱሳት መጻሕፍት ላይ ያለውን ኦርቶዶክሳዊ መረዳትን ያስገኛል።

2. <u>ነገረ ቤተክርስቲያንን ለመረዳት</u>፡- የአበው ትምህርት ቤተክርስቲያን በምድር ያለች የእግዚአብሔር መንግስት መሆኗን ያስገነዝባል። ቤተክርስቲያን በክርስቶስ ደም የተቀደሰች በመሆኗ ሁልጊዜ ወደ ራሷ ክርስቶስ መሄድን ትናፍቃለች። ለዚህም በምድር ሳለች ለአእምሮ የሚመች እውነተኛ ክብር ለእግዚአብሔር የምትሰጥ÷ ስለ ፍጥረትም ሁሉ ሃላፊነት ወስዳ የምትማልድ ÷ ስለ ሰው ሁሉ መዳን የምትጸልይ ÷ የምትጋደል የክርስቶስ አካል መሆኗን በተረዳ የምናውቀው በነገረ አበው ትምህርት ነው። አበው እንደ ግሪኩ ፍልስፍና ያይደለ ከክርስቶስ እንደተቀበሉት ትምህርታቸው ግዙፉን ዓለም ከረቂቁ ÷ ፍጥረትን ከፈጣሪው አንድ የሚያደርጉ ናቸው። ይኸውም ቤተክርስቲያን የህልውናዋ መሠረት የሆነው መሥዋዕቷ፤ ጎበስትና ወይን፤ የሚታይ የሚዳሰስ ሆኖ ጊዚያዊ ሕይወቷን ለእግዚአብሔር ታቀርባለች፤ እርሱም የክርስቶስ ሥጋና ደም አድርጎ ዘላለማዊ ሕይወት በማድረግ ይሰጣታል። እንዲህ ባለ ስስት በሌለበት ፍቅር ሰው ከአምላኩ ጋር ይኖር ዘንድ አበው በቃልም በተግባርም አስተምረዋል።

3. <u>የቤተክርስቲያንን ታሪክ ለመረዳት</u>፡- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘላለማዊ አምላክ ሲሆን ስለ ሰው ልጅ ብሎ በዘመንና በቦታ ተወስኖ ሰው ሆኖ የተገለጠ እንደሆነ ሁሉ አካሉ የሆነች ቤተክርቲያን በጸጋ እግዚአብሔር ከዘመንና ከቦታ በላይ ሆና ዘላለማዊ ብትሆንም በዚህ ዓለም የምትገኝ የእርሱ መንግስት ናትና ታሪክ አላት። የዚህችን ቤተክርስቲያን ታሪክ ያለ አባቶች ለማወቅ መሞከር ከቶ አይቻልም። የክርስቶስ ረድኤት የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የተገለጠባቸው ካለ እነርሱ የቤተክርስቲያንን ማንነትና ታሪክ መረዳት አይቻልም። ቤተክርስቲያን ማኅበርና መንፈሳዊት አንድነት ተብላ መጠራቷ በእነርሱ ነውና። የእነርሱ ሕይወታቸው÷ ተጋድሎአቸው÷ ትምህርታቸው÷ ከመናፍቃን ጋር ተከራክረው መንጋውን መጠበቃቸው የቤተክርስቲያን ታሪክ አካል ነው። ታሪኳን ለመመዝገብ ቤተክርስቲያን ብዙም የተጨነቀች ባትመስልም አውሳብዮስ ዘቂሣሪያን የመሰሉ አንጻራዊነት አተያይ ትክክለኛውን የቤተክርስቲያን ታሪክ የመዘገቡ ሰዎች ነበሩ።

4. የክርስቲያናዊ ኑሮን ለመረዳት፡- በሰው በደል ምክንያት «እሾህና አሜኬላ ይብቀልብሽ።» (ዘፍ 3፡ 18) በተባለች ምድር ላይ ሰው እየኖረ እሾሁ አይውጋኝ ማለት አይችልም። ሰውን ለማዳን ክርስቶስ ሲመጣ ምንም

ንፁሐ ባህርይ፤ ፍጹም አምላክ ሲሆን በፊቃዱ የሰውን ድካም እና ሕማም ገንዘቡ አድርጓል÷ ደክሟል÷ ተርቧል÷ ተጠምቷል÷ በሥጋ ቆስሎ በነፍስ አዝኗል÷ ተክዟል፤ ይህን ሁሉ ተቀብሎ ÷ ይህን ሁሉ ባርኮ ለክርስቲያኖች ሰጥቷል። መስቀሉንም ተሸክመው እንዲከተሉ አዟል። ይህን ሁሉ ድካም ወደ ኃይል÷ ሞትን ወደ ሕይወት ለውጦ በግብር እንድንመስለው አርዓያ ሆኖናል።ይህን በክርስቶስ የሆነውን ሕይወት መማሪያ ሰሌዳዎቻችን አባቶች ናቸው። ነገረ አበው የአበውን ትምህርትና አስተሳሰብ ብቻ ሳይሆን የደረሰባቸውን እንግልት ÷ ስደት÷ እስራት ይህን ሁሉ ስለ ሃይማኖት በአኩቴት (በምስጋና) መቀበላቸውን ያስተምረናል።

5. ነገረ ማርያምን በትክክል ለመረዳት፡- ንጽሕት ሆና ብትገኝ እግዚአብሔር ሰው ይሆንባት ዘንድ የወደዳት እመቤታችን ለኦርቶዶክሳዊው ሥርዓተ አምልኮ ሕይወት ናት።ንፁህ አምላክን የተቀበልንባት ንጽሕት እጅ ድንግል ማርያም ናት። ኦርቶዶክሳውያን አባቶች አምላክ ሰው የመሆኑን ነገር ሲያስተምሩ እሷን ሳያነሱ÷ ለሰው መመኪያ መሆኑዋን ሳይመሰክሩ ማይቻል ነው። በተለይም እነ ቅዱስ አግናጥዮስ÷ ቅዱስ ሄሬኔዎስ÷ ሰማዕቱ ዮስጢኖስ÷ ቅዱስ ኤፍሬም÷ ቅዱስ ያሬድና አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ በስፋት ስለ ክብሯ ÷ ስለ ንጽሕናዋ በሰው ድኅነት ላይ ስላላት ድርሻ በቤተክርስቲያን ያላትን ቦታ በስፋት ማስተማራቸው አሁን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተጀመረ ልል ትምህርት እንዳይደለ ያስረዳል። ይልቁንም ከሐዋርያት ጀምሮ የጸና ኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮ መሆኑን ለመገንዘብ ነገረ አበው ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

ምዕራፍ 2

የቤተክርስቲያንአባቶች

ኦርቶዶክሳዊውን አስተምህሮ በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባር ያስተማሩትን በትምሕርታቸውም መንፈሳዊ ልጆችን የወለዱትን የቤተክርስቲያን መምህራን የቤተክርስቲያን አባቶች እንላቸዋለን።

«አባት» የሚለው መጠሪያ በጳጳሳትና በቀሳውስት ብቻ ሳይወሰን በኦርቶዶክሳዊ ጽሑፎቻቸው ሃይማኖት እንዲጸና ምግባር እንዲቃና ያደረጉ ኦርቶዶክሳወውያን መምህራንን ያጠቃልላል። ቅዱሳት መጻህፍት እንደመሰከሩት አምልኮተ እግዚአብሄርን ይዘው ሌላውም በዚህ እንዲኖር ያደረጉ እግዚአብሔር በቃል ኪዳኑ ያልተለያቸው አብርሃም÷ ይስሐቅና ያዕቆብ «አባቶች» በመባል ይታሰባሉ። (የሐዋ.ሥራ 3÷13)

በነገረ አበው ሊቃውንት ዘንድ አንድን የቤተክርስቲያን መምህር የአባትነት ዕውቅና ለመስጠት አራት መስፈርቶች አሉ።

ሀ. ድርሳናትን የጻፈ፡- ቤተክርስቲያን በተለያዩ ዘመናት ያጋጠሟትን እንግዳ ትምህርቶችን ተቃውሞ ወይም ክርስቲያኖች የቤተክርስቲያንን ትምህርት እንዲረዱ ጽሑፎችን የጻፈ።

ለ. ኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮ፡- በመገለጥ የተገኘውን አምላካዊ ምስጢር ቤተክርስቲያን እንደተረከበችው እርሱም በትምህርቱ ለሌላው ያስረከበ።

ሐ. የሕይወት ቅድስና፡- ኦርቶዶክሳዊውን አስተምህሮ ከሕይወት ነጥሎ ማየት አይቻልም። ስለሆነም ኦርቶዶክሳዊውን አስተምህሮ በጽሑፎቹ በማንጸባረቅ ያስተማረው መምህር የሕይወቱ ቅድስና የቤተክርስቲያንን ማንነት የሚገልጽ ነውና የሕይወት ቅድስና ለአባትነት አንዱ መስፈርት ነው።

መ. ቀደምትነት፡- ይህን መስፈርት በተመከተ የነገረ አበው ሊቃውንት የተለያዩ አስተያየቶችን ይሰጡበታል። ይህም ቀደምትነት እስከ መቼ ያለውን እንደሆነ ማለታችን ነው። አንዳንድ ሊቃውንት እስከ ጉባኤ ኬልቄዶን ነው ሲሉ ሌሎች ደግሞ የደማስቆው ቅዱስ ዮሐንስ እስከተነሳበት እስከ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን ነው

የሚሉም አሉ። የነገረ አበው ሥልጠና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ በቤተክርስቲያን ታሪክ ጉልህ ድርሻ ያላቸውን ቅዱስ ያሬድ ማኅሌታዊና አባ ጊዮርጊስ ሰግላዊን በመጨመር ይመለከታል።

የቤተክርስቲያን አባቶች አከፋፈል

ነገረ አበው ለጥናት ይመች ዘንድ በተለያዩ አከፋፈሎች መመልከት ተገቢ ነው። በዚህ ትምህርት አበውን በነበሩበት ጊዜ÷ በጻፉበት ቋንቋ ÷በነበሩበት ቦታ እና የጽሑፎቻቸውን ጠባይ ለመከፈያነት እንጠቀምባቸዋለን።

1.የነበሩበት ጊዜ (ዘመን)

ከጊዜ አንጻር የቤተክርስቲያን አበው ከኒቂያ በፊት (ቅድመ ኒቂያ) ከኒቂያ በኋላ (ድህረ ኒቂያ) በመባል ለሁለት ይከፈላሉ። ይህም ጉባኤ ኒቂያ የአርዮስን እንግዳ ትምህርት ለማየት የተሰበሰበ ጉባኤ ነው። ከጉባኤው በፊት የነበሩ አባቶች ጽሑፎቻቸው በቀላሉ ሃይማኖትን መመስከር ላይ ያተኮሩ ነበረ። በአንጻራዊ ዕይታ ከኒቂያ በፊት የነበሩ አበው በኋላ ከተነሱት ይልቅ በቀጥታ ለፍልስፍና ትምህርቶች መልስ በመስጠት እና የፍልስፍና ትምህርቶችን የሚሞግቱ ነበሩ። በአንጻራዊ ዕይታ ከኒቂያ በፊት የነበሩ አበው በኋላ ከተነሱት ይልቅ በቀጥታ ለፍልስፍና ትምህርቶች መልስ በመስጠት እና የፍልስፍና ትምህርቶችን የሚሞግቱ ነበሩ።

2.በጻፉበት ቋንቋ

በነገረ አበው ውስጥ የምናያቸው አባቶች ብዙዎቹ በግሪክ የጻፉ ናቸው። ቢሆንም ከግሪክ ሌላ በላቲን በሱርስት በቅብጥ (ዐረብኛ) እና በግዕዝ በመጻፋቸው የጻፉበት ቋንቋ መክፈያ ሆኗል።

3.በነበሩበት ቦታ

በአንጾኪያ እና አካባቢዋ የነበሩ አበው አሉ በቀጲዶቅያ የኖሩ አባቶች አሉ በእስክንድርያም የኖሩ አባቶች አሉ በሰሜን አፍሪካ (በቅርጣግና እና በሂጾ) የኖሩ አባቶች በሮም አካባ የነበሩም አባቶች አሉ።

የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት **(Doctors of the Church)**

የቤተ ክርስቲያን ሊቅ ተብሎ የሚቀጸለው፡-

ሀ. የላቀ እና የጠበቀ የክርስትና ትምህርት እውቀትና ግንዛቤ ላላቸው

ለ. በጽናት ያለመናወጽ ኦርቶዶክሳውያን ለሆኑ እና

ሐ. አርአያነት ያለው የቅድስና ሕይወት ላቸው በጣም ውስን ለሆኑ አባቶች ነው። ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እና ታላቁ ባስልዮስ በቤተ ክርስቲያን ሊቅነት ሲነሱ አንዳንድ መምህራን ቅዱስ አትናቴዎስ እና ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስን ጨምረው አምስቱን ይጠቅሳሉ።

ምዕራፍ -3

የአበው ትምህርት እንዴት ይጠናል?

የአበው ትምህርት ጥናት ሲደረግ የሚከተሉትን ጥንቃቄዎች ማድረግ ያስፈልጋል።

1. አንድን አባት ከኖረበት ዘመን ለይቶ መመልከት ለችግር ሊያጋልጥ ይችላል ስለሆነም ከዘመኑ የነበረው ነገረ ሃይማኖታዊ ሁኔታ መገንዘብ አስፈላጊ ነው።

2. በአንድ አባት ጽሑፍ ላይ ብቻ መወሰንና በዚያ ተመሥርቶ ወደ ድምዳሜ መድረስ አይገባም።

3. ነገረ ሃይማኖታዊ ቃላትና መግለጫዎች እንደ ጊዜ ግብራቸው መመልከት

4. አንድ አባት የተጠቀሰውን ቃል በዘመኑ ከነበሩ ከሌሎች አበው ጋር ማስተያየት (ማነጻጸር) ያስፈልጋል።

<u>የአበው ተጠቃሽነት እስከ ምንድነው?</u>

የማንኛውንም ሰው ትምህርት መመዘኛ ቅዱሳት መጻሕፍት እና የተቀደሰው ትውፊት ናቸው። ስለሆነም የአንድን አባት ተጠቃሽነት ከሁለቱ ጋር የተስማማ እስከ ሆነ ብቻ ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ የትኛውም አባት በፍጹም ሊሳሳት አይችልም ተብሎ አይወሰድም። ቅዱሳን አበው መቼም ቢሆን እንሳሳትም ብለው አያውቁም ይልቁንም በትሕትና ደካማ መሆናቸውን በመግለጥ እነሱም ያጠፉት ካለ ሌሎች እንዲያስተካክሉ ይማጸኑ ነበር። ለምሳሌ ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሳርያ እንዲህ ብሎ ነበር።

“…….If any one has a better interpretation to give, and can consistently with true religion amend what I say. Let him speak and let him ansend, and the Lord will reward him for me.There is no Jealousy in my heart.I have not approached this investigation of these passages for strife and vainglory.I have done so to help my brothers,last the earther Vessels which hold the treasure of God should seen to be deceived by stony hearted and uncircumcised men,whose weapons are the wisdom of folly.”

(St. Basil the Great, Letter Vill.No.7)

“since.then this is our position ,it become your love to be frequent in sending true brothers to visit us who Lobour with the storm ,and more frequently letters of love ,partly to comform our courage partly to correct any mistake of ours,for we confess that we are Liable to numberless mistakes,being men,and living in theflesh.

(St.BasiltheGreat,LetterCClll,No,1)

የነገረ አበው ጥናት ስልቶች

በነገረ አበው ሁለት ዓበይት የአጠናን ዘዴዎች አሉ።

1. *ሳይንሳዊ መንገድ:-* ይህ የአጠናን ዘዴ የአበውን ድርሰቶች ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ወደ ዘመናዊ ቋንቋዎች መተርጎም አስተምህሯቸውን እና አሳቤያቸውን ማጤስ እና መተቸት ላይ የሚያተኩር ነው። ይህን ምዕራባውያን በብዛት የሚከተሉት መንገድ ነው።

2. *መንፈሳዊ መንገድ:-* በአበው ድርሳናት ጥልቅ መንፈሳዊ ይዘት ላይ በመግባትና በቤተ ክርስቲያን ተግባራዊ ሕይወት ላይ እንዲውል በማድረግ የአበውን መንፈሳዊ ብልጽግና መጠቀምና እርሱንም ማጣጣም ላይ ያተኩራል። ይህን መንገድ ምዕራባውያን የሚከተሉት የአጠናን ዘዴ ነው።

ምዕራፍ አራት

የቤተ ክርስቲያን አበው ሕይወት እና ትምህርቶች

ቅዱስ አግናጥዮስ (ለባሴ እግዚአብሔር፤ Theophorus)

ይህ ቅዱስ የወንጌላዊ ዮሐንስ ደቀ መዝሙር አስቀድሞም በሕይወቱ ጌታ አቅፎት ደቀ መዛሙርቱን ያስተማረበት ትልቅ ልጅ እንደሆነ ትውፊት ምስክር ነው። ከቅዱስ ዮሐንስ ጋር ብዙ ሀገሮችን ዞሮ አስተምሯል። በኃላም ሐዋርያው ቅዱሱን በአንጾኪ ላይ የሊቀ ጵጵስና ሹመት ሾሞታል። በዚያ ብዙ ሰዎችን ወደ አምልኮተ

እግዚአብሔር መለሠ የክርስትና ጥምቀቱን አጠመቀ ልቡናቸውንም በቃለ እግዚአብሔር አበራ። አግናጥዮስ ይህ ሁሉ አገልግሎቱን እስመ ሞት ባደረሰው ጠራብዮስ (Trajan) በሚባል አላዊ ንጉሥ ዘመን ፈጸመ።

ቅዱስ አግናጥዮስ ሲነሳ በመከራው ጊዜ ለአብያተ ክርስቲያናት የጻፋቸው ሰባቱ መልእክታት ሊዘነጉ አይችሉም።

መልእክታቱ ለኤፌሶናውያን፤ ለማግኔዥያውያን፤ ለትራሊያውያን፤ ለሮማውያን፤ ለፊላዲልፊያውያን፤ ለሰመርያውያን እና ለቅዱስ ፖሊካርፓስ የተጻፉ ሲሆኑ እነሡም በውስጣቸው ብዙ ሃሳቦችን ይዘዋል። ጥቂት ለመጥቀስ ያህል ፡-

ሀ. ፈርሃ እግዚአብሔርን እምነት እና ፍቅርን ገንዘብ ማድረግ እንዲገባ

ለ. የእመቤታችን ድንግልና የጌታ ልደት እና ሞት ከዶያብሎስ የተሠወሩ ሦስቱ ምሥጢራት ናቸው።

ሐ. ስለ መስቀል ክብር

መ. ከሐሰተኞች መምህራን እና ቁርባንን መቀበል አይገባም ከሚለው እንግዳ ትምህርት መጠበቅ እንዲገባ

ሠ. ኤጲስ ቆጶሱን ማክበር ከእርሱም ጋር በአንድነት መኖር ለእርሱ እና ለቀሳውስት መታዘዝ እንዲገባ

ረ. ከአንድነቱ (ከቤተ ክርስቲያን) በፍጹም መለየት እንደሌለባቸው

ሰ. አንድ መሥዋዕትን ማቅረብ እንዲገባ

ሸ. ብሉይ ኪዳን መልካም ሐዲስ ኪዳን የተሻለ እንደሆነ ለማስተማር

ቀ. የጌታችን ሰውነት እና በሰውነቱ የተቀበለው መከራ ምትሐት ነው ከሚሉ መናፍቃን እንዲጠበቁ

በ.ለእርሱ እንዲጸልዩለት እና ለሌሎች ብዙ ሐሳቦች የያዙ መልእክታትን ለክርስቲያኖች ጽፏል።

ስለ ቅዱስ ቁርባን

ቅዱስ አግናጥዮስ በዘመኑ የነበሩ የክርስቶስን አማናዊ ሰውነት በሚክዱ መናፍቃን ምክንያት ቅዱስ ቁርባን በእውነት የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋው እናደሙ እንደሆነ በሰፊው ያስተምራል። ቅዱስ ቁርባን በሊቁ ትምህርት

ሀ. ለሰውነት መድኃኒት ነው

ለ. በቤተ ክርስቲያን ሆኖ ከእግዚአብሔር ጋር በአንድነት ለመኖር የሚያስፈልግ ምሥጢር ነው።

ሐ. ለሰው የተሠጠ መንፈሳዊ ማዕድ ተብሎ ተገልጿል።

ስለ ቤተ ክርስቲያን

በቤተ ክርስቲያን በምልዓት ከመሠዊያው ዙሪያ በሚሠበሰቡ ምእመናን ትገለፃለች አንድነቱም የማያታየው አምላክ ምሳሌ በሆነው በጳጳሱ ይጠበቃል። የቤተ ክርስቲያን አንድነት እግዚአብሔር አብ ከልጁ ጋር ያለው ፍጹም አንድነት ህያው ምሳሌ ነው። ይህም መንፈሳዊ አንድነት የሚጸናው በክርስቶስ ሥጋ እና ደም ይኸውም በቅዱሱ መሥዋዕት ነው። በቤተ ክርስቲያንም ይህ መሥዋዕት የሚርብባት ብቸኛ ቦታ ናት።

በፍቅር እና በአንድነት የተሰበሰበች በቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ነች። “ኢየሱስ ባለበት ሁሉ ኩላዊት ቤተ ክርስቲያን አለች።” (Symrn.8) እንዲሁም ክርስቲያኖች በእውነት አንድት የሚኖራቸው በእምነት ከኤጲስ ቆጶሳቸው ጋር ሲተባበሩ ነው። ያለ ኤጲስ ቆጶሱም ለአምልኮት መሠብሰብ እንደማይገባ ያስተምራል።

ሰማዕቱ የስጢኖስ (Justin the Martyr)

- ዮስጢኖስ ሰማርያ በምትገኘው የያዕቆብ ጉድጓድ አቅራቢያ የተወሰደ ከአሕዛብ ወገን ወደ ቤተ ክርስቲያን የተደመረ ሰው ነው። የተወለደበትን ጊዜ በትክክል መናገር ባይችልም 114 ዓ.ም አካባቢ ይሆናል ብለው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሊቃውንት ይናገራሉ።
- ወደ ክርስትና ከመምጣቱ በፊት በፍልስፍና ተምራል። በዘመኑ የክርስቲያኖችን ድንቅ የሚሆን ሞትን ያለመፍራታቸውን ነገር እና የብሉይ ኪዳንን እውነተኛነት ተመልክቶ ከክርስትና ጋር ተዋውቋል።ከዚህ በኃላ ወንጌልን አስተማማኝ እና ብቸኛ በጎ ፍልስፍና ነው በማለት ያስተምር ነበር
- የዮስጢኖስ ጽሑፎች ከሁለተኛው ክ/ዘመን ከደረሱን ሌሎች አስፈላጊ ጽሁፎች መካከል ይመደባሉ። በጊዜው የነበረውን በጣዖት አምላኪዎችና በክርስቲያኖች መካከል የነበረውን ክርክር ይጠቁማሉ። ተብለው ሲከሰሱ እንደነበረም በጎዳዮቹ ላይ መልስ የሠጠባቸው ጽሑፎች ያመለክታሉ። ሰማዕቱ ከጻፋቸው ጽሑፎች መካከል የመጀመሪያው ጥብቅና (The First Apolopgy) ሁለተኛው ጥብቅና (The second Apology) እና ከትራይፎ ጋር ምልልስ (Dialogue with Tryho) የሚባሉት መጻሕፍት ሁልጊዜ የሚነሡ ሥራዎች ናቸው። ሌሎች ብዙ ጽሑፎችም በዮስጢኖስ ስም እንዳሉ የነገረ ሊቃውንት ይናገራሉ።
- ዮስጢኖስ እና አምስት ጓደኞቹ በሃይማኖታቸው ምክንያት በ 165 ዓ.ም ተያዙ። በዘመኑ የነበረው ንጉሥ የማርቆስ አውሬሊየስ መምህር ጁልየስ ረስቲከስ ጋር ለፍርድ ቀረቡ ። በዚያም የሃይማኖታቸውን ምስክርነት አሰሙ። ዮስጢኖስም “ትምህርቶችን ሁሉ ተምሬአለሁ በመጨረሻ ግን

የክርስቲያኖች የሆነውን እውነተኛውን አስተምህሮ ተቀብያለሁ”(Martyrdom of Justine ANF,VOlL,page305) “ቢፈረድብንም በጸሎት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያድነናል ይህ ፍርድ ለእኛ ድኅነት ይሆናል። አስፈሪ ከሆነውም የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍርድ ጋር ሲነጻጸርም ያጽናናል።” (Martyrdom of Justine ANF,VOlL,page306) በማለት ሰማዕቱ ዮስጢኖስ መለሠ የእርሱ ጓደኞችም እናንተ የወደዳችሁትን አድርጉ እኛ ክርስቲያኖች ነንና ለጣዖት መሥዋዕትን አናቀርብም። በማለት ጸንተው ሁሉም በሰማእትነት ሞቱ።

ስለ ቅዱስ ቁርባን

ይህ በእኛ ዘንድ ያለ መብል ቁርባን ይባላል። ከእርሱም እኛ የምናስተምረውን ትምህርት እውነት ነው ብለው ካመኑ ለኃጢአት ሥርየት እና ለዳግም ልደት ከክርስቶስ ጋርም አንድ ለመኖር ከተጠመቁ ሰዎች ውጪ ሊቀበሉት የማይቻላቸው ነው። ይህን እንደተራ ጉበስትና መጠጥ የምንቀበለው አይደለም በሥልጣነ እግዚአብሔር ስለ እኛ ድኅነት ሥጋ እና ደም በሆነው በእርሱም ቃል የተቀደሰውን የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ እና ደም ነው እንጂ ጌታ ጉበስቱን አንስ እንደ አመሠገነ ይህን ለታሰቢያዬ አድርት ይህ ሥጋዬ ነው እንዳለ እንዲሁም ጽዋውን አንስቶ በማመስገን ይህ ደሜ ነው በማለት ለእነርሱ ብቻ እንዳቀበለ ሐዋርያት ጽፈዋቸው እኛ ጋር የደረሠው ወንጌላት ይነገሩናል።

- ከዚህ በተጨማሪም ቡበሉይ ኪዳን ስለ ክርስቶስ መምጣት ስለ ሞቱ እና ትንኤው የተነገሩ ትንቢቶች ሁሉ እንደተፈጸሙ በተለያዩ ቦታዎች በጽሑፎች አስቀምጠዋቸዋል። ነፍሰ እግዚአብሔርን ማየት እንደማችል በባሕሪዋ ኢመዋቲ እንዳልሆነች ያስተምራል።

ቅዱስ ኤፍሬም ሶሪያዊ

ከአሕዛብ ወገን ናቸው ከሚባሉ እናቱ እና አባቱ በ 306 ዓ.ም አበካባቢ እንደ ተወለደ ይነገራል። በንጽሕና በዲቆንነት እና በመምህርነት አገልግሏል። የግሪክ ቋንቋን አያውቅም ነበር ከጉባኤ ኒቂያ በኃላ ግን ከባስልዮስ ዘቂሣርያ ጋር ሲገናኙ የባስልዮስ ቋንቋ ጽርዕ እንደ ተገለጠለት አበው ይናገራሉ። ቅዱስ ኤፍሬም ብዙ አቀራረባቸው ማራኪ የሆኑ ቅኔያዊ (Poetic) የእምት ምሥክርነት ጽሑፎች ባለቤት ነው። በዝማሬ መልስ (Hymns) ብዙ ስራዎች አሉ። ከእነርሡም ስለ እምነት (Hymns on faith) እና ስለ ገነት (Hymns on Paradise) የሚባሉት ሥራዎች ቡብዙዎች ዘንድ ተጠቃሽ ናቸው።

<u>የእግዚአብሔር ራሱን መግለጥ</u>

- የሰው ኃሊና የማይደርስበትን አምላክ ሰው በመጠኑም ቢሆን ይረዳ ዘንድ ሥውር የሆነው አምላክ ሁለት ምስክሮችን አዘጋጀ። የመጀመሪያው ፍጥረት ወይም ተፈጥሮ (Nature) ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ቅዱሳት መጻሕፍት ናቸው።
- በፈጣሪ እና በፍጡር መካከል መሠረት የሌለው የአለት ገደል ያህል ልዩነት እንዳለ ያስተምራል። ስለሆነም የእግዚአብሔር ራሱን መግለጥ ለሰው አስፈላጊ እንደሆነ ይነገራል።

  “ እግዚአብሔር ራሱን ይገልጥልን ዘንድ ፈቃዱ ባይሆን ከፍጥረት እርሡን ወደ ማወቅ ስለእርሡም አንዳች ነገር እንኳ ለመረዳ የሚችል አይኖርም ነበር።”

<u>የሥጋ ክብር</u>

- ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም ለጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ፈተና ከነበረው ከምንታዌ አስተሳሰብ የራቀ ሆኖ እናየዋለን።ከዚህ ጋር በተገናኘ ግዙፉን ዓለም ክፍ ረቂቁን አለም መልካም ነው በሚሉ ሰዎች አሳብ አይስማማም።

- በመጀመሪያ ደረጃ ሥጋ የእግዚአብሔር ፍጥረት በመሆኑ መልካም መሆኑን ይናገራል ቅዱስ ጳውሎስ ሥጋቸው በእናንተ በሚያድር መንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ አታውቁምን (1 ቆሮ 6፡19) ሥጋ ለማደሪያነት በእግዚአብሔር የተመረተ መልካም መሆኑን ያስረዳል። በተጨማሪም ሰውን ለማዳን ሲመጣ ሥጋን ለበሰ (Nativity 9:2) ተብሎ መነገሩ በምን ያህል ክብር እንዳከበረው ያመለክታል።

“ምንጩ ክፉ ቢሆን ነሮ የእግዚአብሄር ቅድሳት የሚሆኑ ምሥጢራቱን በሰው ሥጋ አይጨምርም ነበር።” (Heresies 43:3)

ስለዚህም በቅዱስ ኤፍሬም ትምህርት ሥጋ እና ነፍስ እኩል የከበሩ አስፈላጊዎች ናቸው።

“ለራስህ ማደሪያ ይሆንህ ዘንድ ፈጥረኸዋልና ሥጋ አንተን ያመሠግናል።በመምጣትህ ለራስህ አጭተሃታልና ነፍስም ለአንተ ትገዛለች።” (Heresies 17:5)

<u>ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜ</u>

- በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙት የተለያዩ የእግዚአብሔር ስሞች እና ምሳሌዎች ሁሉ የሰው እና የራሱ እግዚአብሐየር መገናኛ ናቸው። እግዚአብሔር ከፍቅሩ የተነሣ ራሱን ከልዕልና ወደ ሰው መረዳ (Understanding) ዝቅ አድርገዋል። ስለሆነም ሰው ከዚህ ታላቅ ዕድል ለመጠቀም ሁለት ነገሮች ይጠበቁበታል። የመጀመሪያው መጻሕፍ ውስጥ የተነገሩትን ስሞችን እና ምሳሌዎችን በቁሙ ወስዶ ከመተርጎሙ ስህተት መጠበቅ ነው። ሁለተኛው ደግሞ የአንባው አመለካከት የተቃና መሆን አለበት። መጻሕፍትን በፊት ወደ ጎሊናው ከገቡ ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር ከሚጣሉ ሃሳቦች ጋር ሆኖ ቢያነሳ እግዚአብሔርን ወደ ማወቅ ሊያደርሰው አይችልም።
- ቅዱሳት መጻሕፍት በሊቁ አመለካከት በኩነት ዓለም ለመዳን አምላክ ካደረገው ሥጋዌ በፊት የነበሩ ሥጋ ተብለዋል ። ይህም ማለት ሥጋዌ የማይዳሰሰውን እና የማይታየውን አምላክ የሚዳስስ ቃል

(ቋንቋ) መነገሩ (መገለጡ) ነው። ከኅሊና በላይ የሆነው ወደ ሰው ኅሊና መረዳ ዝቅ አለ መባም ስለዚህ ነው።

- በሃይማት ሳይሆን የክርስቶስን አምላክነቱን መረዳ እንደማይቻልእንዲሁ በትሕትና እና በእምነት ሆነው መጻሕፍትን ካነቡ የመጻሕፍቱ መንፈሳዊ ትርጓሜ ላይ መድረስ የማይቻል ነው።

ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ኦርቶዶክሳዊነትን በማስጠበቅ ጉልህ ድርሻ ስላለው በብዙዎች ዘንድ ተወዳጅ አባት ነው። በኒቂያ ጉባኤ ላይ መምህሩ እለ እስክንድሮስን ተከትሎ በመሄድ አርዮሳዊውን ትምህርት በአንደበቱ ውድቅ አድርጎ ኦርቶዶክሳውዊውን ትምህርት በማሰማት አርዮስን ረቷል። ከዚም በኃላ ስለ ክርስቶስ ቀዳማዊነት፤ የባሕርይ አምላክ ስለመሆኑ ብዙ ጽሑፎችን ጽፏል። አምስት ጊዜ ስደት ደርሶበታል። ለኢትዮጲያ ቤተ ክርስቲያን ፍሬምናጦስን አቡነ ሰላማ በማለት የመጀመሪያውን ጳጳስ የሾመ እርሱ ነው።

- በኒቂያ ጉባዔ አንቀጽ ሃይማኖት ውስጥ ያለውን "ዘዕሩይ ምስለ አብ በመለኮቱ" (Homoousion to patri) ተብሎ የተገለጸውን ሐረግ ለረጅም ጊዜያት ኦርቶዶክሳዊ መሆኑን መሥክሮአል።

በእንተ ተሠግዎቱ ለቃል (ስለ ቃል ሰው መሆን)

- ሊቁ የአምላክ ሰው መሆን በእርሱ ከተፈጸመው ድኅነት ጋር በጥብቅ የተገናኘ መሆኑን ያስረዳል። በሥጋ የተገለጠው አምላክ ከዓለም መፈጠር አስቀድሞ ከዘለዓለም ከአብ የተወለደ የባሕርይ አምላክ በኃለኛውም ዘመን ከእመቤታችን ማርያም የተወለደው የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን በግልጽ ያስተምራል።ለመወለዱ ጥንት በሌለው አስቀድሞ ዓለም ሳይፈጠር በመለኮቱ ከአብ

በተወለደ ዳግመኛም እኛን ለማዳን በኃላ ዘመን ከቅድስት ድንግል ማርያም በተወለደ በእግዚአብሔር ልጅ እናምናለን። ይላል።(ሃይ.አበው.ዘአትና.ገጽ 68)

- እግዚአብሔር መልካም ሰውንም የሚወድ ስለሆነ በአርአያው የፈጠረውን የሰው ዘር ለማዳን ወደደ በሰው በደል ምክንያት የመጣውን የሞት ቅጣት እንዲሁ ቢያሳልፍ (ቢያስቀር) የእውነት አባት የሚባል እግዚብሔር ሐሰት ሊታሰብበት ይሆናል። ስለሆነም ሰው የሚያስፈልገው ካሣ ይፈጸምለት ዘንድ አስፈላጊ ነው። ይኸውም ከሞት ባርነት ነፃ መውጣት ነው። እነዚህን ሁሉ ሁኔታዎች እግዚአብሔር ቃል ሰው ሆኖ ፈጸማቸው። በሰው በደል ምክንያት ሰው በባሕሪው ያለን እግዚአብሔርን የመምሰል ጸጋ ቢያበላሽ እግዚአብሔር አብ ልጁን አቀረበ። ይህን እኛን ስለመውደዱ አደረገው። በእርሡ ሞት ሁሉ ይሞት ዘንድ በኃይሉም የሞት ሕግ ይሻር (ይጠፋ) ዘንድ። (On the Incarnation 34)
- በሰውነቱ መሥዋዕትነት ሁለት ነገሮችን ፈጸመ መንገዳችንን ያበላሻውን የሞት ሕግ ሻረ። ዳግመኛም ለሕይወታችን ሐዲስ ጀማሪ ሆነ ይኸውም ተስፋ ትንሣኤን በመስጠቱ ሆነ ። በሰው ምክንያት ሞት በሰው ሁሉ ላይ ሥልጣንን አገኘ ቃል ሰው በመሆኑ ዳግም ሞት ተደምስሶ እንደገና ሕይወት ተገኘ ።(On the Incarnation 37)
- ሊቁ ከእርሡ ዘመን አስቀድሞ ስለነበረው ታላቅ አባት ቅዱስ እንጦንስ ሙሉ ታሪክ ጽፏል።

<u>የቀጰዶቅያ አባቶች (ቅዱስ ጎርጎርየሥ ዘኑሊስ ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሳርያ እና ቅዱስ ጎርጎርዮስ</u>

<u>ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ</u>

- በ335 ዓ.ም አካባቢ በቂሣርያ እንደተወለደ የቤተ ክርስቲያን ጸሐፊዎች ይናገራሉ። ቤተሰቦቹ ባለጸጎች ነበሩ። በዲዮቅልጢያኖስ ጭፍጨፋ ጊዜ አያቶቹ ወደ ጳንጦስ ተራራማ ክፍል ሸሽተው ሄደዋል በዚያም ብዙ ችግርና መከራ ተቃቁመዋል። የባስልዮስ ዘቂሣርያ ጎርጎርዮስና ማክሬና ወንድም ነው።

የቅዱስ ጎርጎርዮስ ትምህርት በእንተ መንፈስ ቅዱስ

- በሊቁ ትምህርት መንፈስ ቅዱስ በአንዳች እንኳ ከአብ እና ከወልድ የማይለይ ከእነርሡም ፋር አንድ የሆነ ነው። መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር የሆነ (ከአብ)የክርስቶስም መንፈስ የሚባል እንደሆነ ያስተምራል። መንፈስ ቅዱስ ከአብ በመሥረጽ በወልድ የተሠጠ (Holy sprit proceeds from the father through the son) በማለት መንፈስ ቅዱስ ከአብ እንደሠረጸ በግልጽ ያስተምራል።

ስለ ሰው ተፈጥሮ

- በቅዱስ ጎርጎርዮስ ትምህርት ሰው ከሚታየው ፍጥረት ሁሉ በላይ የከበረ ነው። ይህ ፍጥረት ሁሉ ለሰው እንደተፈጠረ ያስተምራል። አንድ ሰው የሚወደውን እንግዳ ወደ ቤቱ ሊያስገባ (ሊጋብዝ) ቢል ቤቱን ያስጌጠዋል። ዕቃዎቹን ያማልል እንዲሁ እግዚአብሔር ሰውን ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ ወደዚች ዓለም ሊያመጣው ሲል አስቀድሞ የሚያስፈልገውን ሁሉ ፈጥሮለት ነው። ይህም ምን ያህል ሰው እንደነበረ ያመለክታል በማለት ይናገራል።
- ከዚህ በተጨማሪ ሊቁ ስለ ነፍስ እና ትንሣኤ እንዲሁም ስለ ድንግልና ጽፏል።

ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሳርያ

- በ316 ዓ.ም አካባቢ እንደተወለደ ይነገራል ።የትውልድ ቦታው ቂሣርያ ነው በማለት የታሪክ ምሁራን ያስቀምጣሉ የንግግር ጥበብን እን ፍልስፍናን ትምህርት በትጋት በቂስጥንጥንያ ተማረ።

- በዩኒሚየስ (አርዮሳዊ መናፍቅ ነው) ላይ የተቃውሞ ጽሑፍ አለው አርዮሳውያን የሚጠቅሷቸውውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በማንሳት ያብራራበት ጽሁፍ አለው።
- የመጻሕፍት ቃለት ያብራራበት የትርጓሜ ሥራዎችም አሉት።
- ምናኔያዊ (Ascetical) እና ስብከታዊ ጽሑፎችም አሉት።

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ

- ከወንጌላዊው ዮሐንስ ቀጥሎ ነባቤ መለኮት ተብሎ ይጠራል። በቁስጥንጥንያ ጉባኤ ላይ “ቃል ሥጋን ብቻ ነሣ” የሚለውን የአቡሊናርዮስን እንግዳ ትምህርት በመቃወም ኦርቶዶክሳዊውን አስተምህሮ አንፀባርቋል። በክርክሩም ላይ ቃል ከሰው ሥጋ ብቻ የነሣ ቢሆን እግዚአብሔር በፈጸመው ማዳን ላይ ምን ያህል ለውጥ አምጥቶ ሃይማኖትን እንደሚያስጠል በሰፊው ተናግሯል። “ያልነሣውም አላዳነውም” በማለት ቃል ሥጋን ስለነሣ ትንሣኤን አለመበስበስ አደለ፤ ነፍስንም ስለነሣ ከሲኦል ባርነት ነፍሳትን አወጣ በማለት ያስተምራል።
- ስለ ታላቁ አትናቴዎስ እስክንድርያዊ ሲናገር “አትናቴዎስን ሳመሰግን መልካም ምግባርን ማመስገኔ ነው።ስለ መናገር እኔ መልካም ምግባርን ማወደስ አንድ ናቸው” በማለት ለሊቁ ያለውን ክብር ይገልፃል።
- የቂሣርያው ቅዱስ ባስልዮስ ቀብር ላይ እሱ እና ቅዱስ ባስልዮስ “በሁለት አካላት ያሉ አንድ ነፍስ” እንደሆኑ ፍቅራቸውን ይገልጻል።
- ስለ ክርስቶስ ልደትም ሲናገር “ክርስቶስ ተወልዷልና አመስግኑት ከሰማይ መጥቷልና ውጡና ተቀበሉት።በምድር ላይ ታይቷልና ደስ ይበላችሁ። ሰማያት እና ምድር ደስ የሰማያዊ የሆነው ክርስቶስ በሥጋ ተገልጧልና። በመንቀጥቀጥና በደስታ ደስ ይበላችሁ።መንቀጥቀጥ ስለ ኃጢአታችሁ ምክንያት

ነው። ደስታም ስለተሰጣችሁ ተስፋ ነው። ቀዳማዊ የሆነውን የማይመልከው ማነው? ዘለዓለማዊ የሆነውን የማያከብረው ማነው?"

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ

- በሶሪያ ዋና ከተማ በአንጾኪያ በ 347 ዓ.ም ተወለደ። አባቱ በሶሪያ የሚገኘው የሮም የጦር መኮንን ነበር። አባቱ በሕፃንነቱ ስለሞተ ዮሐንስን በምግባር የማሳደጉ ሓላፊነት የእናቱ ነበር። ብዙ የጋብቻ ግብዣዎች ወደ እናቱ ቢመጡም እርሷ ግን ሁለተኛ ጋብቻን አይሆንም በማለት ጸናች። ከልጅነት ጀምሮ በምግባር የሚታነጽበትን ትምህርት ብታስተምረውም እስኪጎለምስ ድረስ የክርስትናን ጥምቀት አልተጠመቀም ነበር። የንግግር ጥበብን በመማር በንግግር አዋቂነቱ ታዋቂ ሆነ።ከ 381-398 ዓ.ም በዲቁና በቅስና እና በሰባኪነት በአንጾኪያ ያለችውን ቤተ ክርስቲያን አገለገለ።
- እንደ ዮሐንስ አፈወርቅ ፍሬያማ ሰባኪ እና ጸሐፊ በቤተክርስቲያን ታሪክ አልተነሣም። ታላቅነት ከክርስቲያናዊ ትህትና ጋር የተባበረለት ሊቅ ነው። በዚህም የሰባኪያን ንጉሥ ተብሏል።
- ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ስብከቶቹ እና ጽሑፎቹ ተግባራዊ የክርስትና ልምምድ ላይ በጥልቀት የሚያተኩሩ ናቸው። ወንድምን መውደድ የክርስትና ሕይወት ነፍስ እንደሆነ ይናገራል። ከማኅበራዊ ኑሮ አንጻር ክርስትና እንዲሉ ያስተማረ አለ ለማለት ያስቸግራል።
- ስለ ክህነት ክብር ስለ አጋንንት ሀይል በአንጾኪያ ስለሚገኙ ሰዎች ሁኔታ በሰፊው ጽፏል።
- ሊቁ በብዙዎች የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ላይ ትርጓሜያትን (Exegesis) ሠርቷል።

ስለ ካህናት እና ሕዝባውያን ግንኙነት

- እንደ ሊቁ ትምህርት በቤተሰብ ውስጥ የሴቶች ድርሻ በወንድ ራስነት ውስጥ ሆነው በፍቅር እና በትህትና አገልግሎታቸውን መፈጸም እንደሆነ ሁሉ ይኸው አካሄድ ለቤተ ክርስቲያንም አገልግሎት የሚሠራ ነው።"ጳጳሳትና ቀሳውስት ራስን መሥዋዕት አድርጎ በሚያቀርብ ፍቅር ቤተ ክርስቲያንን

ይመሩ ዘንድ ይገባቸዋል።" ክርስቶስ አካሉ ቤተ ክርስቲያንን መጀመሪያ እንደመሠረታት ካህናት ይህን እንዴት እንደሚያደርጉ ሊቁ ሲያስተምር "ቃለ እግዚአብሔርን ልናስተምር ሥልጣነ ክህነትን አገኘን እንጂ ሥልጣናችንን በሌሎች ላይ ልናሳይ አይደለም።" (NONF,Homily Xi On Ephesions) በማለት ይናገራል። ዳግመኛም "ካህን ራሱን እና ቤተሰቡን በሚገባ የሚገዛ መሆን አለበት። ራሱ ይህ ካልሆነ ሌሎች ፍትወታትን እኩያትን እንዲያስወግዱ እንዴት ይናገራል። (NPNF, Homily II on Titus):: ሦስተኛውም "ካህን ትሁት መሆን አለበት። እርሡ የማይጠቅም መሆኑ የተጠራበት አገልግት ግን ታላቅ እንደሆነ ሁልጊዜ ማወቅ አለበት።" በማለት ያስተምራል።

ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ

- በእስክንድርያ መንበር ላይ 24 ተኛው ፓትርያርክ ቅዱስ ቄርሎስ ነው። አባቱቻችን ኦርቶዶክሳውያን ነገረ ሃይማኖት ከቀደሙት አበው ተቀብሎ በስፋት በማስተማሩ ማኅተመ አበው ይሉታል። በ 378 ዓ.ም አካባቢ በታህታይ ግብፅ ተወለደ።
- ጲላዲዮስ ጠያቂ ሆኖ ከሊቁ ጋር ያደረገው ምልስ አንዱ ተጠቃሽ የቅዱስ ቄርሎስ ሥራ ነው። ጽላድዮስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌል ላይ "ኦሪት እና ነቢያት ልፈጽም እንጂ ልሽር አልመጣሁም።" (ማቴ 5:17-18) ብሎ የተናገረው "እግዚአብሔርን በእውነት እና በመንፈስ ሆነው ሊሰግዱለት ይገባል" (ዮሐ:4-34) ከሚለው ጋር የሚጋጭ ስለመሰለው በዚህ መነሻነት ያደረጉት ምልልስ ነው።
- ቅዱስ ቄርሎስ ሌላ የሚነሣበት በነገረ ሥጋዌ ላይ ያሳየው ጽኑዕ ኦርቶዶክሳዊ አቋም ነው። ንስጥሮስ የሚባል የቁስጠንጢንያ ሊቀ ጳጳስ በቃል ሥጋ መሆን ላይ ምንታዌን (ሁለትነትን) ማተማር ሲጀምር አምላክ በሥጋ የተወለደባትን ድንግል ማርያምን ወላዲተ አምላክ አትባልም ሲል ሊቁ ቅዱስ ቄርሎስ እሷን ወላዲተ አምላክ አለማለት ከእርሷ የተወለደውን የክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት መካድ እንደሆነ ተናገረ።ቃል ከእመቤታን ሥጋን ሲነሣ እና የራሱ አድርጎ ሲዋሐድ የቃል ግንዘብ ለሥጋ የሥጋ

ገንዘብ ለቃል በመሆኑ (Communcatio idioatiom) ሥጋ የባሕርይ አምላክ ሆነ። ስለሆነም አምላክ ሰው ሲሆን ከሁለት ባሕርያት በፍጹም ተዋሕዶ አንድ ባሕርይ ሆኖ ነው እንጂ ከተዋሕዶ በኋላ ሁለትነት የለም። ሊቁ በጊዜው በጻፈበት በጽርዕ ቋንቋ ይህን ቀመር (Miaphysis tu Thou Logou sesarkomene) ብሎ ገልጾታል። ከዚያ በኋላ የኢትዮጲያ ሊቃውንት ይህን ሥርው ቃል በማለት የተዋህዶን ትምህርት አጽንተዋል።

- ሊቁ የመለኮትና የሥጋን ተዋሕዶ በጋለ ብረት መስ ያስተምራል። የጋለ ብረት ቢመታ እሳቱ(ግለቱ) እንደማይለየው ክርስቶስም መከራን ሲቀበል ንስጥሮስ እንደሚለው መለኮት የተለየው አይደለም።

ቅዱስ ያሬድ

- በ 505 ዓ.ም በአክሱም አካባቢ ተወለደ። የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጓሜና ሥርዓተ ማኅሌቱን አስተባብሮ ደረሠ ታላቅ ሊቅ ነው። አባቱ አብዩድ ወይም ይስሐቅ እናቱም ክርስቲና ወይም ታውክልያ ተብለው ይጠሩ ነበር። ቅዱስ ያሬድ ጌድዮን ከሚባለው አጎቱ ዘንድ ጠቅላላውን መንፈሳዊ ትምህርቱን እየተማረ ሊቅነቱና ቅድስናው ከዕለት ወደ ዕለት እየተሟላ ሄደ ወደ ፍጹም ብቃት ስላደረሠው በቀጥታ ከመላእክት በሚሰማው ድምፅ ተመሥጦ ጸዋትወ ዜማን ለመድረስ ቻለ።
- ይህንንም እርሡ ራሱ “ዋይ ዜማ ዘሰማዕኩ በሰማይ እመላእክት ቅዱሳን” በማለት ገልጾ በዜማ ተናግሮታል። በዚህም ወደ ሦስተኛው ሰማይ ወጥቶ የማይመረመር ነገርን ያየ የሰማ ቅዱስ ጳውሎስን መስሎታል።(2 ቆሮ 12-1-5)
- ሊቁ ጸዋትወ ዜማን ከ 540-560 ዓ.ም ባለው ጊዜ ደርሷል። በታላቁ ጻድቅና ሐዋርያ በአቡነ አረጋዊ ስም በደብረ ዳሞ በተሠራው ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ያሬድ ተገኝቶ “ይሔውጽዋ መላእክት እንተ በሰማያት ይሔውጽዋ መላእክት እስመ ማኅደረ መለኮት ዖድክዎ ዖድክዎ ወርኢኪ ሥነ ሕንጓዛ

ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን፤ በሰማያት የዚች ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን የሕንፃዋን ማማር አየሁ።" ሊቁ እንዲህ ማለቱ ሥርዓተ ሠሣዕናን አብነት አድርጎ ነው።

- ሊቁ አስቀድሞ ወደ ነበረበት ወደ አክሱም እንደተመለሰም "ቅድስት ውብዕዕት ስብሕት ውብርክት ክብርት ወልዕልት" በሚል መነሻ ተነሥቶ አንቀጸ ብርሀን የተባለ አዲስ ድርሰት ደርሶ እመቤታችንን በዜማ አመስግኗታል።
- ሊቁ በመንፈስ ቅዱስ ረድኤት ድጓ፣ ጾመ ድጓ፣ ዝማሬ፣ መዋሥዕት እና ምዕራፍን እንዲሁም አንቀጸ ብርሃንን በመድረስ ለኢትዮጲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ አምልት ጉልህ እና ታላቅ አስተዋጽኦ አድርጓል።
- በእነዚህም መንፈሳውያን ሥራዎቹ የእግዚአብሔርን ልዕልና፣ መጋቢነቱን፣ የክርስቶስ መድኃኒትነት፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም ስለ ዓለም ከንቱነት ያስተምራል። ለምሳሌ ያህል፡-

  "ኩሉ ኃላፊ ወፈላሲ ወኩሉ ከመልብሰ ይበሊ አንተስ እግዚኦ ለዓለም ትንብር ማለት ዓለም ከነ ፈቃዲ በውስጢም ያለው ሁሉ ኃላፊ እንደሆነ እግዚአብሔር ግን ለዘለዓለም እንደሚኖር ይመሠክራል።" (ጾመ ድጓ)
- ቅዱስ ያሬድ ከዚህ ሌላ የዜማ ምልክቶችን ለቤተ ክርስቲያን አበርክቷል።

አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ

- ✓ ኢትዮጲያዊው ቁርሎስ በ 1357 ዓ.ም በቦረና ወረዳ ሰግላ በተሰኘች ቦታ ተወለደ።አባ ጊዮርጊስ ሰማዕቱ ጊዮርጊስን በመማፀን የተወለዱ በመሆናቸው እንደ ሰማዕቱ የእውነት ምስክር እንዲሆኑላቸው በመመኘት ስማቸውን ጊዮርጊስ ብለው ጠርተዋቸዋል።

- ✓ የብዙ መንፈሳዊ ሥራዎች ባለቤት የሆኑት አባ ጊዮርጊስ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የሚታወቁትን ብዙዎቹን መናፍቃንና የምንፍቅና ትምህርቶቻቸውን የዘለፉበት መጽሀፍ መጽሐፈ ምሥጢር በብዙዎች ዘንድ ይታወቃል።
- ✓ ከዚህም ሌላ ሞኅተ ብርሃን፣ መጽሐፈ አርጋኖን፣ ውዳሴ መስቀል፣ መጽሐፈ ብርሃን፣ እንዚራ ስብሐት፣ መጽሐፈ ሰዓታት፣ መዓዛ ቅዳሴ፣ ጸሎተ ፈትቶ፣ ውዳሴ ሐዋርያትና የሐዋርያት ማኅሌት የተሰኙ ጽሑፎች አሏቸው።ጽሑፎቻቸው ብዙዎቹ የሥርዓተ አምልኮት ቃላተ አክብሮት (Divotional) ሲሆኑ የተወሰኑት ደግሞ ነገረ ሃይማኖታዊ ምስክርነት ያላቸው መጻሕፍት ናቸው።
- ✓ ሊቁ በዘመኑ የተነሣውን ቢቱ ለሚባለው ኢትዮጲያዊ መናፍቅ መልስ ሰጥቷል። ቢቱ ክርስቶስ ዳግመኛ ለፍርድ ሲመጣ አብ እና መንፈስ ቅዱስ አይመጡም በማት እንግዳ ትምህርት አስተምሯል። አባ ጊዮርጊስ ይህ ሊቀበሉ የማይገባ ክፉ ትምህርት ስለሆነ መጻሕፍትን እየጠቀሰ መልስ ሰጥቶበታል።

  “እግዚአብሔርሰ ገሃደ ይመጽእ ወአምላክነሂ ኢያረምም እሳት ይነድድ ቅድሜሁ” (መዝ 49:3) የሚለውን ጊዜ በቀደመ አኗኗሪ ተቀመጠ በመልክ ሁለት አልሆነም በባህርዩም አልተጨመረበትም የካህናት አለቆች የሰውን ልጅ በሀይል ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይ ደመናም ሲመጣ ታዩታላችሁ እንዳላቸው በወለደው ቀኝ ተቀምጦ ሁለተኛ ይመጣል።እነሆ በቀኙ ከሚቀመጥ ከልጁ ጋር የአብ የመምጣቱ ዜና ታወቀ ስለሚዳሰስ እርሱ ግን ስለማይዳሰስ ስለሚያይ እርሱ ግን ስለማታይ ኃይል ተባለ።” (መጽ ምሥጢር የደብረ ዘይት ምንባብ ቁ. 9. ገጽ 93)
- ✓ ሊቁ ለእመቤታችን ያለው ፍቅር ታላቅ ነው:: “እንዚራ ስብሐት” በተሰኘው መጽሐፉ እመቤታችንን አመስግኗታል። በመጽሐፉ በአንድ ቦታ ፍጥረት ሁሉ ለእርሷ እንደተፈጠረ ሲያመለክት፡-

  “በእንቲአኪ ፈጠረ እግዚአብሄር ምድረ ወሰማያተ

  ፀሐየ ወወርኃ ወከዋክብተ::”

በማለት “በእንተ እግዝእትነ ማርያም ተገብረ ኩሉ ዓለም፤ ዓለም ሁሉ ስለ እመቤታችን ተፈጠረ።” (መቅድመ ተአምረ ማርያም) ከሚለው የመጽሐፍ ቃል ጋር የሚተባበር ምስጋናን ተናግሯል። ይኸም በምሥጢር ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ “ሁሉ ለእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል።” (1 ቆላ 1-15-16) ካለው ጋር የሚስማማ ነው።እግዚአብሔር ቃል ካለ እመቤታችን ሊወለድ፤ ክርስቶስም ሊባል አይችልምና በአንድ ገጸ ምሥጢር ሲታይ ዓለም ለክርስቶስ ተፈጠረ ቢባል ክርስቶስን ከእመቤታችን ነጥሎ ማየት አይቻልምና “ዓለም ለእመቤታችን ተፈጠረ” ያሰኛል።

ዳግመኛም ሊቁ ጌታ ከእመቤታን ተወለደ በመገለጡ ምክንያት የሰው ባሕርይ በተዋሕዶ በአብ ቀኝ እንደተቀመጠ ከእመቤታችን አንጻር ይናገራል።

“ለዘመጽአ እምሕፅነ አቡኑ ወረዶ

ስነኪ ፈቲዎ ወሞገሰኪ ፈቂዶ

ዘየርኪ ርስኖ ወአግመርኪ ነዶ

ተመሰልኪ ጽርሐ ወተሰመይኪ ማኅፈዶ

ኦ ድንግል እንተ አልብኪ ተብዕዶ

በየማነ አብ ሥጋ ዚአኪ ነበረ በተዋሕዶ” በማለት ይመሠክራል።